ABCON – Research & Consulting
Social, marketing & opinion researchers

AFRO BAROMETER 1999-2019
20 years of giving voice to Africans

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ጥቅምት 20 2013 ዓ.ም

# የፕሬስ መግለጫ

## እጅግ የሚበዙ ኢትዮጵያውያን ዲሞክራሲን ይደግፋሉ፤ ተጠያቂነት ያለው አስተዳደርን ይሻሉ፡፡

በጣም ከፍተኛ ብልጫ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ሲደግፉ፤ ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ ስርዓቶች ማለትም የአንድ ፓርቲ አገዛዝ፣ ወታደራዊ መንግስትና በአንድ ሰው የሚዘወር አገዛዝን እንደማይቀበሉ አዲሱ የአፍሮ ባሮሜትር የጥናት ውጤት አሳይቷል፡፡

አብዛኞቹ ኢትዮጵያዊያን ለዜጎች ተጠያቂ የሆነ መንግስት፤ በፓርላማ ቁጥጥር የሚደረግበትና ተጠያቂ የሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲኖር ! ተመራጭ ባለስልጣናት ለተመረጡበት አካባቢ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይሻሉ፡፡

ግማሽ ያህሉ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ብዙ ጉድለት ያለበት ዲሞክራሲ ወይም ምንም ዲሞክራሲ የማይታይበት ሀገር አድርገው እንደሚመለከቱ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ እንዲሁም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ዲሞክራሲ በሀገራቸው እየተተገበረበት ባለበት መንገድ ላይ እንዳልረኩ ገልፀዋል፡፡

### ዋና ዋና ግኝቶች

- እጅግ በጣም ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ኢትዮጵያውያን (90 በመቶዎቹ) ከማንኛውም መንግስታዊ ስርዓት ይልቅ ዴሞክራሲን ይመርጣሉ፡፡ በተጨማሪ በጣም ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ዜጎች ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ ስርዓቶችን አይፈልጉም፡- የአንድ ፓርቲ አገዛዝ (77%)፣ ወታደራዊ መንግስት (76%) እና የአንድ ሰው አገዛዝን (84%)፡፡ (ለዝርዝሩ ግራፍ 1ን ይመልከቱ)

- ወደ 2/3ኛ የሚጠጉ (ማለትም 65 በመቶዎቹ) ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ሳያማክር ውሳኔዎችን በራሱ ከሚወስን መንግስት ይልቅ ለዜጎቹ ተጠያቂ የሆነ መንግስት እንዲኖር ይፈልጋሉ፡፡ (ግራፍ 2)

- ከአስሩ ኢትዮጵያዊያን ሰባቱ (69 በመቶዎቹ) ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግበት ይሻሉ፡፡ (ግራፍ 3)

- ወደ 4/5ኛ የሚጠጉ (79 በመቶዎቹ) ኢትዮጵያዊያን ተመራጭ አመራሮች የመረጣቸውን ህብረተሰብ ሀሳብ ማድመጥና ፍላጎቱንም መፈፀም ይገባል አሉ፡፡ (ግራፍ 4)

- ግማሾቹ (50 በመቶዎቹ) ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን "በብዙ ችግር ውስጥ ያለ ዲሞክራሲ" ወይም "ምንም አይነት ዲሞክራሲ የሌለባት" አድርገው ይመለከታሉ፡፡

- አብዛኞቹ (54 በመቶ) ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ዲሞክራሲ እየተተገበረ ባለበት መንገድ ደስተኞች አይደሉም፡፡

## የአፍሮ-ባሮሜትር ጥናቶች

አፍሮ ባሮ-ሜትር አፍሪካ ላይ ትኩረት ያደረገ ገለልተኛ የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችን የሚሰራ ተቋም ነው። ይህ ተቋም ታማኝ የሆኑ መረጃዎችን በዋናነት ዲሞክራሲ፣ አስተዳደርና የኑሮ ጥራት ላይ በማሰባሰብ የካበተ ልምድ አፍርቷል። ተቋሙ ሰባት ዙር ጥናቶችን በ38 ሀገራት ላይ ከ1999 እስከ 2018 እ.ኤ.አ መስራት የቻለ ነው፡ ፡ ስምንተኛ ዙር ጥናት በ2019/2020 የተካሄደ ሲሆን፤ ከ35 ሀገራት በላይ ተሳትፈውበታል። የአፍሮ ባሮ-ሜትር ጥናቶች የሚያካሄዱት በዋናነት በገፅ-ለገፅ ቃለ-ሙጠይቅ ሲሆን፤ የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደት የጥናቱ ተሳታፊዎች በመረጡት አካባቢያዊ ቋንቋ ይሆናል። ጥናቱ የሚካሄደው ወካይ የሆነ የናሙና መጠን በመመደብ ነው።

በፍሪደም ሀውስ ድጋፍ የኢትዮጵያ አፍሮ ባሮ-ሜትር ቡድን የተመራው በአብከን-የአማካሪ ድርጅት ነው። ጥናቱ የተካሄደው 2400 ቃለ-መጠይቆችን ዕድሜአቸው 18ና ከዚያ በላይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በማሳተፍ፤ መረጃው ከታህሳስ እስከ ጥር 2020 እ.ኤ.አ ተሰባስቧል። የናሙናው መጠን በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰራና ወካይነት ያለው ሲሆን፤ የስህተት ህዳጉ +/-2 መቶኛና የአስተማማኝነት ደረጃው 95 በመቶ ነው። የአፍሮ ባሮ-ሜትር ጥናት ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የተካሄደው በ2013 እ.ኤ.አ ነበር።

## የግራፎች ዝርዝር

**ግራፍ 1፡ ኢትዮጵያ በምን መልኩ ትተዳደር እንዲሁም ምን አይነት መንግስት ይኑራት?** ኢትዮጵያ | 2020




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርበላቸው የነበረው ጥያቄ፤**

ቀጥሎ ከቀረቡት ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አመለካከት ወይም ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው? (በሀሳብ 1 የሚስማሙ የመቶኛ ድርሻ)

ሀሳብ 1: ለማንኛዉም ዓይነት መንግስት ዲሞክራሲ አስፈላጊ ነው።
ሀሳብ 2: አንዳንድ ጊዜ ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ መንግስት አስፈላጊ ነው።
ሀሳብ 3: እንደ እኔ ላለ ሰዉ የትኛዉም ዓይነት መንግስት ቢኖር ለውጥ የለውም

ሀገርን የማስተዳደሪያ ብዙ የተለያዩ መንገዶች አሉ። ቀጥሎ የማቀርብሎትን ሀገር የማስተዳደሪያ አማራጮች ይቃወማሉ ወይስ ይደገፋሉ?

- አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ ነው ለምርጫና ስልጣን ለመያዝ ሊፈቀድለት የሚገባው
- ወታደሩ ሀገር የማስተዳደር ስልጣን መያዝ አለበት
- የምርጫና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠፍቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማንኛዉንም ነገር በራሱ መወሰን ቢችል

(የመቶኛ ድርሻው "እቃወማለሁ " ወይም "በጣም እቃወማለሁ " ያሉትን በተናጥል ይይዛል)

Copyright ©Afrobarometer 2020

**ግራፍ 2፡ የመንግስት ተጠያቂነት እና ውጤታማነት** | ኢትዮጵያ | 2020




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርቦላቸው የነበረው ጥያቄ፤**

ከሚከተሉት አስተያየቶች/ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አስተያየት/ ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው?

ሀሳብ 1: በሚሰራው ነገር ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ባንችልም ማስፈፀም የሚችል መንግስት መኖሩ የበለጠ አስፈላጊ ነው።

ሀሳብ 2: ምንም እንኳን ዉሳኔዎችን የበለጠ ዘገምተኛ የሚያደርግ ቢሆንም ፤ መንግስትን ተጠያቂነት ማድረግ መቻል ለዜጎች በጣም አስፈላጊ ነው።

**ግራፍ 3፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ አባላት ቁጥጥር ይደረግበት ወይስ በራሱ የሚወስን ይሁን** | ኢትዮጵያ | 2020




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርቦላቸው የነበረው ጥያቄ፤** ከሚከተሉት አስተያየቶች/ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አስተያየት/ ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው?

ሀሳብ 1: ጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግስት የግብር ከፋዮችን ገንዘብ እንዴት ስራ ላይ እያዋለው እንደሆነ ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት በቋሚነት ሊገልጽለት ይገባል ።

ሀሳብ 2: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ድርጊቶቹ ለማሳመን ጊዜዉን ከሚያጠፋ ይልቅ ሀገሪቱን በማሳደግ ላይ ሙሉ አትኩሮቱን ማድረግ አለበት።

**ግራፍ 4፡ ተመራጭ አመራሮች የመረጣቸውን ህብረተሰብ ፍላጎት መፈፀም አለባቸው ወይስ የራሳቸውን ፍላጎት ማዳመጥ** | ኢትዮጵያ | 2020



**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርቦላቸው የነበረው ጥያቄ፤**

ከሚከተሉት አስተያየቶች/ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አስተያየት/ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው?

ሀሳብ 1: ተመራጭ አመራሮች የመራጮቻቸውን ሀሳብና አስተያየት መስማትና ፍላጎታቸውን መፈጸም አለባቸው።

ሀሳብ 2: ለሀገሪቱ የሚያስፈልገውንና የተሻለ ነው የሚሉትን ለመወሰን ተመራጭ አመራሮች የራሳቸውን ሀሳብ መከተል አለባቸው።

**ግራፍ 5፡ የዲሞክራሲ ተፈፃሚነት ደረጃ** |ኢትዮጵያ | 2020




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች የቀረበው ጥያቄ፤** በእርስዎ አስተያየት፣ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ በምን ደረጃ ዲሞክራሲያዊ ነች ይላሉ?

**ግራፍ 6፡ በዲሞክራሲ ላይ የተሳታፊዎች እርካታ** |ኢትዮጵያ | 2020




## For more information, please contact:

Mulu Teka
National Investigator
ABCON – Research & Consulting
Tel +251 973 077 414 , +251 115 531 470, +251 115 521 696, +251 115 537 061
mulu.mtg@gmail.com / info@abconltd.et
Addis Ababa, Ethiopia

**Visit us online at:**
www.afrobarometer.org
www.abconltd.et

Follow our releases on #Voices Africa.

/Afrobarometer @Afrobarometer Afrobarometer